**አርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች የቤተሰብ ህይወት ትምህርት ላይ የወላጆች በምርጫ የማስተማር ፎረም - 1ኛ ክፍል**

የተማሪው ስም : ________________________________ ስልክ ቁጥር: ___________________
የአስተማሪው ስም: ________________________________ ቀን : ______________________

እኔ እዚህ ያለሁት ከተዘረዘሩት አላማዎች ውስጥ ልጄ እንዳይሳተፍ የምፈልግበትን ምርጫ እንዳደርግ ነው። ልጄ እንዳይሳተፍ በማደርግባቸው አላማዎች ላይ፣ ልጄ ያለምንም ተፅእኖ አማራጭ አሳይመንቶች እንደሚሰጡት ተረድቻለሁ። ልጄ አሳይመንት በሚሰራበት እና ለአሳይመንቱ ውጤት በሚሰጥበት ወቅት፣ በትምህርት ቤቱ ህጎች እና ፖሊሲዎች መመራት እንደሚጠበቅበት ተረድቻለሁ።

<u>**መንገዶች**</u>**:** እባክዎ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አላማዎች ላይ ልጅዎ እንዳይሳተፍበት የሚፈልጉትን ነገር ካለ ምልክት ያድርጉበት።

___ **1.1 ተማሪው ስኬትን እና ስለራሱ መልካም የሆነ ስሜት ን እንዲለማመድ ይደረጋል።**
<u>መግለጫ</u>: አስተማሪው ተማሪዎች በትምህርታቸው ስኬታማ እንዲሆኑ፣ የአካላቸውን ሁኔታ መቀበል እንዲችሉ፣ ተደጋጋሚ ሁኔታዎችን እንዴት መያዝ እንዳለባቸው እንዲያውቁ እና በቡድን ሆነው መስራት እንዲችሉ በክፍል ውስጥ ጥሩ ሁኔታ መፍጠሩን ይቀጥላል። ወላጆች ስኬታማ ልምምድ እንዲኖራቸው፣ በራሳቸው እንዲተማመኑ እና ቤት ውስጥ መልካም የስነ-ልቦና ልምምድ እንዲኖራቸው ይበረታታሉ።

___ **1.2 ተማሪው ከሌሎች የሚያገኘው አክብሮት ማግኘቱን ይቀጥላል።**
<u>መግለጫ</u>: በትምህርት ቤቱ ውስጥ ያሉ አስተማሪዎች እና ሌሎች ትልልቅ ሰዎች ልጁን በደንብ መስማታቸውን እና ስሜቱን እና ምርጫውን መቀበላቸውን ይቀጥላሉ፣ ተማሪው ከሌሎች ተማሪዎች አካላዊ፣ ስነ-ልቦናዊ እና ስሜታዊ ጉዳት እንዳይደርስበት በክፍል ውስጥ ጥበቃ ማድረግ ናቸው። ከባድ የሆኑ ሁኔታዎች ለምሳሌ በመጫወቻ ስፍራ በጉልበተኛ ተማሪዎች የሚደርሱ ነገሮችን የምንወያይበት ይሆናል።

___ **1.3 ተማሪው የእሱ ወይም የእሷ ባህሪ በሌሎች ላይ ያለውን ጉዳት እና የሌሎች ባህሪዎች ደግሞ በእሱ ወይም በእሷ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት እንዲያውቅ**
<u>መግለጫ</u>: አስተማሪው የተማሪዎች ባህሪ በሌሎች ላይ የሚያደርሰን ጥሩም ይሁን መጥፎ ጉዳት እና የሌሎች ባህሪም እንዴት እነርሱን እንደሚጎዳ ተገቢ በሆነ ቋንቋ ይገልፃል።ተማሪው ሌሎች ማክበር፣ ስሜታቸውን ማክበር እና መልካም የሆኑ የስነ-ልቦና ባህሪዎችን መለማመድ እንዳለበት ይማራል። ተማሪው የእርሱ ባህሪ የሌሎችን ስሜት ሊጎዳ እንደሚችል እንዲያውቅ ይደረጋል።

___ **1.4 ተማሪው የቤተሰብ አስፈላጊነትን እና የተለያዩ አይነት ወላጆች እንዳሉ መረዳቱን ያሳድጋል።**
<u>መግለጫ</u>: ትኩረቱ ወላጆችን መውደድ ወይም ቤት ውስጥ ሀላፊነት ያለባቸውን ታታላቆችን መውደድ ሲሆን ማንኛውንም አይነት ቤተሰብ ያጠቃልላል። ተማሪው ከመዋእለ-ህፃናት ጀምሮ ስለተለያዩ የቤተሰብ አይነቶች እንዲያውቅ ድረጋል ይህም የቤተሰብ ጠቀሜታን፣ ከቤተሰብ ጋር ያለ ግንኙነት ዋጋ እንዳለው እና እና አይነታቸውን እስከ አንደኛ ክፍል ድረስ እንዲረዳ ነው። የቤተሰብ አይነቶች የሚከተሉት ናቸው፡ ሁለት ወላጆች ያሉበት፣ ቤት ውስጥ ከእናት እና አባት ውጪ ሌሎች ዘመዶች የሚኖሩ ከሆነ፣ነጠላ ወላጅ ያለበት

ቤተሰብ፣ በማደጎ የሚያሳድጉ ቤተሰቦች፣ የእንጀራ ወላጅ ያለበት ቤተሰብ እና ሌሎች ቅልቅሎች ያለበት ቤተስብ ናው።

___ **1.5 ተማሪው የቤተሰብ አባላትን እና ለቤተሰቡ ስኬታማነት ያላቸውን አስተዋፅኦ እንዲለይ ይደረጋል።**

<u>መግለጫ</u>: ቤተሰብ በስኬታማነት እንዲሰራ ምን አይነት ስራዎች መሰራት አለባቸው የሚለው ላይ ትኩረት ያደርጋል።ከሚሰሩት ስራዎች ውስጥ ለምሳሌ ያህል ምግብ ማቅረብ፣ መጠለያ መስጠት፣ ልብስ ማቅረብ፣ አስፈላጊ ለሆኑ ለሌሎች ነገሮች ገንዘብ መሰጠት፣ ፍቅር እና እንክብካቤ መስጠት ይህም ትልልቅ ወይም አካላዊ እና ስነ-ልቦናዊ ችግር ያለባቸውን የቤተሰብ አባላትን ማገዝ እና ለመጫወት እና ለመደሰት ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንደምሳሌ የሚጠቀሱ ናቸው።

___ **1.6 ተማሪው ሰዎች እና ሌሎች አጥቢ እንስሳት ልጆች እንደሏቸው እና ልጃቻቸውም ጡት እንደሚመክቡ እንዲያወቁ ይደረጋል።**

<u>መግለጫ</u>: ከዚህ አላማ ጋር የሚመሳስሉ ፅሁፎች በመፅሀፍት፣ በጋዜጦች፣ ፊልሞች ላይ፣ ቪድዮዎች እና ሌሎች ነገሮች ላይ ይገኛሉ ይህም በትምህርት ቤቱ ተቀባይነት ያገኙ ናቸው። የአጥቢ እንስሳትን ባህሪ ለማሳየት የቤት እንስሳትን ልንጠቀም እንችላለን። የቤተሰብ የየቀን ስራዎችን በሚማሩበት ወቅት ወላጆች ይህንን አላማ እንዲደግፉ ይበረታታሉ።

___ **1.7 ተማሪዎች ስለሰውነት ክፍል እና ስራዎቻቸው በሚማሩበት ወቅት ትክክለኛውን ቃል ይጠቀማሉ።**

<u>መግለጫ</u>: ሳይንሳዊ የሆኑ ቃላቶች ልክ እንደ ሽንት፣ የሆድ እቃ እንቅስቃሴ፣ ብልት እና ጡት የመሳሰሉት ቃላት በየእለት ህይወታቸው በሚያደርጓቸው ስራዎች ውስጥ እንዲያውቋቸው ይደረጋል እንጂ በቀጥታ አይማሩትም። ወላጆችም በቤት ውስጥ ትክክለኛውን ቃላት እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ።

___ **1.8 ተማሪው የራሱን ወይም የራሷን የደስታ፣ የሀዘን እና የንዴት ስሜት በአስተማሪዎቻቸው ላይ ይገልፃሉ።**

<u>መግለጫ</u>: አስተማሪዎች እያንዳንዱን ተማሪ በግል የደስታ፣ የሀዘን እና የንዴት ስሜቶቻቸውን በመረዳት እና እንዲገልፁ በማድረግ ያግዛሉ። ተማሪዎች ስሜታቸውን እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው እግዛ ይደረግላቸዋል። ግላዊ የሆኑ ነገሮች ሲከሰቱ፣ አስተማሪዎች ወላጆችን ለማግኘት ይገደዳሉ ይህም የተማሪውን የግል ችግሮች በጋራ ሆነው ለመፍታት ነው። ቀና የአእምሮ ጤንነት ልምምዶች ይተገበራሉ።

___ **1.9 ተማሪው ስሜቱን ወይም ስሜቷን እንዴት መቆጣጠር እንዳለባቸው ግንዛቤ ይሰጣቸዋል**

<u>መግለጫ</u>: ትኩረቱ ተማሪው ስሜት ከባህሪ ጋር የተለያየ እንደሆነ እንዲረዳ ማድረግ ነው። አስተማሪው ተማሪው ስሜት ባህሪ ላይ ተፅእኖ እንዳለው እንዲደረ፣ እያንዳንዱ ሰው የራሱን ባህሪ መቆጣጠር እንደሚችል እና ስሜቱን መግለፅ የሚችልባቸውን መንገዶች እንዲያውግ ይረዳዋል። ሁሉም ስሜቶች አስፈላጊ እንደሆኑ ተማሪው እንዲረዳ ማድረግ ለአስተማሪው አስፈላጊ ነገር ነው። ስሜትን መግለፅ የሚያስችሉ ትክክለኛ መንገዶች፡ እንቅስቃሴ ማድረግ፣ ጨዋታዎች፣ በቀጥታ በቃል መግለፅ፣ ስእል፣ ሙዚቃ፣ ዳንስ፣ ተረት ማገገር እና የፈጠራ ድራማዎች ናቸው። ቀና የአእምሮ ጤንነት ልምምዶች ይተገበራሉ።

___ **1.10 ተማሪው የእሱ ወይም የእሷ ባህሪ ምክንያታዊ ውጤቶችን ያውቃል።**

<u>መግለጫ</u>: ተማሪው በየቀኑ በየቀን ህይወቱ ውስጥ ተገቢውን የሆነ ምርጫ እንዲያደርግ እና የምርጫውን ውጤ (መልካም እና ወጥሮ ውጤት) እንዲያወቅ እድል መሰጠት አለበት።በሁሉም የእድሜ ክልል ውስጠ ሀላፊነት የተሞላበት ውሳኔ ማድረግ እና መልካም የእእምሮ ጤንነት የሚገኘው በምርጫ ላይ እድልን

በመስጠት ነው። በዚህ የክፍል ደረጃ ላይ የገቢ የሆኑ ምርጫዎችን በምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ከቀረቡት ምግቦች ውስጥ መምረጥ፣ ከተለያዩ የመማሪያ እና የስራ ክፍሎች ውስጥ ምርጫ ማድረግ እና በትምህርት ወቅት የሚሰጡ ስራዎችን ለመስራት የሚከተሏቸውን ቅደም ተከተሎች መምረጥ ናቸው። ተገቢ ከሆኑ ቅደም-ተከተሎች ውስጥ ለምሳሌ ያህል የፈሰሰን መጠጥ መጥረግ ወይም ቅጣትን መቀበል ናቸው።

___ **1.11 ተማሪው አካላዊ ፍቅር የጓደኝነት፣ የክብረ-በአል ወይምየአፍቃሪ ቤተሰብ መገለጫ እንደሆነ ይገነዘባል።**

<u>መግለጫ</u>: ተማሪው ፍቅርን ለአንድ ሰው ወይም ለቤተሰብ አባላት መግለጥ አስፈላጊ እንደሆነ እንዲያስታወስ ይደረጋል። ተማሪው ተገቢ እና ተገቢ ያልሆኑ ፍቅር መግለጫዎችን ልዩነቶቻቸውን እና በግለሰብ የአእምሮ ጤንነት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት መረዳት ይጀምራል። የግላዊነት እና ለራስ እና ለሌሎች ገደብን የማድረግ አስፈላጊነት ይነገራል እና ተማሪው የግሉን እና የሌሎችን ገደብ እንዴት እንደሚያከብር እንዲየሳይ የሚረዳ መሳሪያ ይሰጠዋል።

___ **1.12 ተማሪው ከቤተሰብ አባላት፣ ጎረቤቶች፣ መንገደኛ እና ሌሎች ሰዎች ለሚደርስበት ተገቢ ያልሆነ ምላሽ እንዴት መመለስ እንዳለበት ይገለፅለታል።**

<u>መግለጫ</u>: የመልካም (ቀና፣ ጤነኛ) እና የመጥፎ (አሉታዊ፣ ጤነኛ ያልሆነ) ንክኪዎች ይገመገማሉ እና አሉታዊ ለሆኑ ነገሮች ምላሽ የሚሰጡበትን መንገድ ይቀርብላቸዋል። ተገቢ የሆኑ የግንኙነት መሳሪያዎች ልክ እንደ ስልክ እና ኢንተርኔት አጠቃቀም ይነገራዋል። ተማሪዎች ለሚያምኑት ተለቅ ላለ ሰው እንዴት መናገር እንዳለባቸው ይማራሉ ይህም ክስተቱ በተከሰተበት ወቅት ያገኙትን ወላጆችን፣ አስተማሪዎችን፣ ሚኒስቴሮችን፣ አያቶችን ወይም አሳዳጊዎችን የሚያጠቃልል ይሆናል።

**ትምህርት ቤታችሁ በወሰነው ቀን መሰረት ይህንን ቅፅ በመሙላት ለርእሰ-መምህሩ እባክዎን ያስረክቡ**

የወላጅ/የአሳዳጊ ፊርማ: ________________________________________ ቀን: __________